# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

## 7

- ★ ፊት ለፊት የማይጋፈጡትን ከበስተኋላ
- ★ በአብዮቱ ሂደት ላይ የመደቦች መንሸራተትና ትግል
- ★ ወዝ አደሩ ይናገር
- ★ "ምን መደረግ አለበት" ሌኒን
- ★ የታሪክ ቁስ አካልነት

ሐምሌ ፴ - ፲፱፻፷፯ ዓ.ም.

## ለውይይት መነሻ

**አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቁጥር ፩ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው ።**

# የታሪክ ቁስ አካልነት

### ፫ኛ ትምህርት—ኮን- ዓ-

በኅብረተሰባችን ውስጥ በየጊዜው ብዙ ለውጦች እናያለን ። ይህ ደግሞ አያስገርምም ። በዲያሌክቲክስ እምነት ማንኛውም ነገር ከትንሿ አቧራ አንሥቶ እስከ ፀሐይና ከዋክብት ድረስ ባለማቋረጥ በመንቀሳቀስ ላይ ነው ። ኅብረተሰብም ከዚህ ከጠቅላላ እንቅስቃሴ የተለየ አይደለም ። ሊሆንም አይችልም ። ከመቶ ሃምሳ ዓመት ወዲህ ያለውን የአገራችን ሁኔታ እንኳ ብንመለከት ዘመነ መሣፍንት ፤ የአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ፤ የአፄ ዮሐንስ ዘመን፤ የምኒልክ ዘመን ፤ የጣልያን ጊዜና የአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን እየተባለ ሲነገር እንሰማለን ። ዛሬ ደግሞ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጭቆናንና ብዝበዛን በማስወገድ ሌላ የራሱ የሆነ ሥርዓት ለመመሥረት በመታገል ላይ ይገኛል ።

እዚህ ላይ እንግዲህ ማንም ሰው ሁለት ጥያቄዎችን መጠየቁ አይቀርም ። እነዚህን ለውጦች የሚያመጣቸው ነገር ምንድን ነው ? ለመሆኑ በአጋጣሚ የተጠረቃቀሙና ፤ የተግተለተሉ ለውጦች ናቸው ወይንስ ለውጡ የሚመራው በተወሰነ ሕጎችና የተወሰነ አቅጣጫ ይዞ ነው ? ሁለት መልሶች አሉ ። አንዱ የሐሊናውያን (አይዲያሊስቶች) ሲሆን ፤ ሌላው የማቴርያሊስቶች መልስ ነው ።

በመጀመሪያው የአይዲያሊስቶችን መልስ እንመልከት ። ወደኢትዮጵያ ታሪክ እንመለስና የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች የሚያስረዱንን እንይ።አሁንም «ጣልያን ለምን መጣ ? » ሲባል «የዓድዋን ቂም ለመበቀል» ይሉናል ። ሌላስ ምን ምክንያት ነበረው ? ሲባል ደግሞ «የውጫሌ ውል አንቀጽ ፲፯ የትርጉም ስሕተት ተደርጎ በዚህ ሳቢያ በመጣው አለመግባባት ነው» ይሉናል ። አፄ ቴዎድሮስስ ለምን ሸፈቱ ? ሲሏቸው «የኅቸው ደግሞ እንደዚህ ነው ። ኮሶ ታይቷቸው ሳሉ አማታቸው የስንብት አንድ እግር ሥጋ ልከው ስላዋረዱዋቸው ሸፈቱ» ። ግራኝ መሐመድስ ለምን ተነሣ ? «እሱ ደግሞ አፄ ልብነ ድንግል የሰላም ዘመን ሰልችቷቸው (ጦር አምጣ) እያሉ መሬት በአለንጋ ሲያስገርፉ እግዜር ጦር ላከባቸው ወዘተ ....» ይሉናል ። እንግዲህ ከኛ ታሪክ ጸሐፊዎች ስልት ስለታሪክ ሁለት ነገሮች እናያለን ።

<u>አንደኛ</u> ፤ ታሪክ በግለሰቦች ስሕተት ፤ ድፍረት ዐዋቂነት ፤ አላዋቂነት .... የሚንቀሳቀስ የአጋጣሚ ድርጊቶች ጥርቅምሽ ነው ማለት ነው ። ለምሳሌ የውጫሌ ውል አንቀጽ ፲፯ በደንብ ተተርጉማ ብትሆን ኖሮ .... የዓድዋ ጦርነት ፤ ከዚያም የጣሊያን ወረራ ፤ የተንቤን ፤ የእንደርታና የማይጨው ጦርነቶች ፤ የአምስት ዓመቱ የጭቆናና የወረራ ዘመን ባልነበረም ነበር ማለት ነው ።

<u>ሁለተኛ</u> ፤ የታሪክ ሒደት የአጋጣሚ ድርጊቶች ጥርቃሞና ዝብርቅርቅ እንጂ ምንም ዓይነት የሚከተለው ቋሚ ሕግ የለውም ማለት ነው ።

ሌላ የታሪክ መመልከቻ ዘዴ ደግሞ አለ ። ይኸኛው የአይዲያሊስቶችን አቀራረብ ከሁለቱም አንፃር ይቃወማል ። (ቁስ አካላዊና ዲያሌክቲካዊ የሆነ አስተሳሰብ ነው) ከላይ ያነሣናቸውን ጥያቄዎች ሲመልስ ፤ ለውጦችን የሚያመጣቸው የኅብረተሰቡ መሠረት የሆነው የኤኮኖሚ አቋም እየተለወጠ በመሔዱ መሆኑን ይገልጻል ። የሰዎቹ ድርጊት ፤ የሰዎቹ እምነት ራሱ የሚፈልቀው ከቁስ አካል ማለት ከኅብረተሰቡ መሠረት ከሆነው ከኤኮኖሚው በመሆኑ ፤ ይህ የኤኮኖሚ መሠረት እየተለወጠ ሲሔድ የሰዎች እምነትና ድርጊትም አብሮ እየተለወጠ ሰዎችን ታሪክ ፈጻሚዎች ያደርጋቸዋል ማለት ነው ። ባጭሩ ይኸኛው ወገን ታሪክን በማቴሪያሊዝም አንጻር ይመለከታል ማለት ነው ።





ሁለተኛ ደግሞ ፤ የታሪክ መለዋወጥ የሚከተላቸው የተደነገጉ ሕግጋት አሉ ወይ ? ሲባል ፤ አዎን አሉ ብሎ ይመልሳል ። ምክንያቱም ከላይ እንዳልነው የዲያሌክቲክስ የለውጥ ሕጎች አጠቃላይ የሆኑና ማንኛውም ዓይነት ለውጥ የሚከተላቸው ሕጎች በመሆናቸው ነው ። እነዚህ ሕጎች በኅብረተሰብ ታሪክ ለውጥ ላይ እንዴት እንደሚሠሩ ዝቅ ብለን እናያለን ።

ለምሳሌ ወደጣልያኑ ወረራ ብንመጣ በዲያሌክቲክስ የለውጥ ሕጎች የሚመራው ታሪክ አጥኝ ይህንን ሁሉ ጦርነት በዚያች በአንቀጽ ፲፯ ላይ በተደረገችው የትርጉም ስሕተት ላይ አይቆልለውም ። እርግጥ እሷ ነገሩን ጭራ ይሆናል ። ነገር ግን ቢበዛ ሰበብ እንጂ የጦርነቱ ምክንያት ልትሆን አትችልም ። መሠረታዊው ምክንያት ግን በዚያን ጊዜ የነበረው የጣልያን የኤኮኖሚ ሁኔታ ወደ ጦርነት የሚገፋፋ ስለነበረ ነው ። ጉዳዩ እንዲህ ሆኖ ነው እንጂ የአንቀጽ ፲፯ን ትርጉም አስተካክሉ ያንን ሁሉ ዕልቂት ማገድ ይቀል አልነበረም? ጣልያን የዓድዋንም ሆነ የማይጨውን ጦርነት እንድታነሣሣ የገፋፋት መሠረታዊ ነገር ፤ ኤኮኖሚዋን ለማበልጸግ የግድ ቅኝ ግዛት (እንደሌሎቹ ኢምፔሪያሊስት ጓደኞቿ ) መያዝ ስለነበረባት ነው ኢትዮጵያም ደግሞ ደካማና ያልሠለጠነች አገር ስለነበረች ለወረራ የተመቸች ነበረችና ነው ።

ባጭሩ ፤ ይኸኛው የታሪክና የኅብረተሰብ ለውጦችን በሚያጠናበት ጊዜ ፤ የለውጡን ምክንያት በሚመለከተው በኩል ማቴሪያሊስት የሆነ አስተሳሰብ አለው ። ሁለተኛ ደግሞ ፤ በኅብረተሰቦችም ቢሆን የሚደረገው ለውጥ ጠቅላላውን የዲያሌክቲክስን የለውጥ ሕጎች ይከተላል ብሎ ያምናል። ባጭሩ የታሪክ ቁስ አካልነት ማለት ኅብረተሰቦችን ቁስ አካላዊና ዲያሌክቲካዊ በሆነ መንገድ የምንመለከትበት መነጽር ነው ማለት ነው ።

<u>፩ኛ/ የማርክስ ፍልስፍና ስለኅብረተሰቦች ማቴሪያሊስት የሆነ አስተሳሰብ አለው ።</u>

ማንኛውም ኅብረተሰብ የተሟላ ኑሮ ለመኖር ቁሳቁሳዊና «መንፈሳዊ» ፍላጎቶቹን ማርካት አለበት ። ሁለቱም ያስፈልጉታል ። ማንኛውም ሰው ፤ ማንኛውም ኅብረተሰብ ከእንጀራ ሌላ (እዚህ ላይ እንጀራ ስንል ምግብን ብቻ ሳይሆን ፤ በጠቅላላው ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ቁሳቁሳዊ ነገሮች ልብስ ቤት ወዘተ . . . ጨምረን ነው) ብዙ ነገሮች ያስፈልጉታል ። የተሟላ ኑሮ ከተፈለገ የመንፈስ ምግብ ልንላቸው የምንችለው ሙዚቃ፤ ሥዕል ፤ ሥነ ጽሑፍ ፍልስፍና ፤ ወዘተ . . . እነዚህም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው ። ለዚህ ነው ለምሳሌ ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም የሚለው አነጋገር ትክክል የሚሆነው ።

የማርክስ ቁስአካላዊ ፍልስፍና ይህንን አይክድም ። ነገር ግን ማርክስ <u>ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም</u> ካለ በኋላ ልብ የማንላትን መሠረታዊ ሀቅ ይጨምራል ። ይቺም <u>ሰው ያለ እንጀራ አይኖርም</u> የምትለዋ የማቴሪያሊስቶች መሠረታዊ ሀቅ ነች ።

በነማርክስ አስተሳሰብ ሰዎች በሳይንስ ወይም በፖለቲካ በሥነጽሑፍ ወይም በሙዚቃ ፤ በፍልስፍና ወይም በሥዕል ፤ ከመራቀቃቸው በፊት መብላት ፤ መጠጣት ፤ መልበስ ፤ መጠለል . . . ባጭሩ መኖርና ለዚህም ደግሞ ማምረት መቻል አለባቸው ።

እንግዲህ ማርክስ የሚለው በጣም ቀላል ነገር ነው ። <u>ኅብረተሰብ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ግን ደግሞ ያለእንጀራም አይኖርም</u> ። ከአሳብና ከቁስአካል ማንኛውም ቀዳሚ ነው ። ለሚባለው መሠረታዊ የፍልስፍና ጥያቄ አሳብ ከቁስአካል የተገኘ የቁስአካል ተቀጢላ ነው የሚለው የማርክስ ፍልስፍና በኅብረተሰብ በኩልም የማያጠራጥር ተመሳሳይ መልስ አለው ። በኅብረተሰብም ከአሳብ ፤ ከስነጽሑፍ ፤ ከፍልስፍና ፤ ከፖለቲካ . . . . ተቀዳሚውና መሠረታዊው ነገር ቁስአካላዊ የሆነው ኅብረተሰቡ ለእንጀራው የሚያደርገው ትግልና የኢኮኖሚው አቋሙ ነው ማለት ነው ።

የማርክስ ፍልስፍና በዚህ አያቆምም ፤ ሰው ያለእንጀራ አይኖርም የሚለውን አሳብ አጥብቆ ይይዛል ። ይህም ማለት ሰው ኑሮውን ፤ አስተሳሰቡን እምነቱን ፍልስፍናውን የሚቀይስለት ለእንጀራው የሚያደርገው ትግል ነው ማለት ነው ። የዕለት እንጀራውን ሳያፈራ መፈልሰፍ አይችልም ።

እንግዲህ በቁስ አካላዊነት አስተሳሰብ ቁስአካል ከሕሊና ይቀድማል ። እንዲያውም አሳብ ከቁስ አካል የፈለቀ የቁስአካል ተቀጢላ ነው እንደሚባለው ሁሉ በኅብረተ ሰብም ውስጥ የሰዎች አስ

ተሳሰብ የተጨባጩ ኑሮዋቸው ተቀጢላና የሱ ነፀ ብራቅ ነው ማለት ነው ።

በሀገራችን አንድ ተረት አለ ። « ሰው ምን ይመስላል ቢለው ኑሮውን » አለ ይባላል ። ሰው እንዴት ያስባል ቢባል እንደኑሮው ማለት ይቻላል ። ማንኛውም ሰው ኅብረተሰብ ነክ ከሆኑ ጥያቄዎች ላይ የሚኖረው አስተሳሰብ በኅብረተሰቡ ኢኮኖሚ ውስጥ ባለው ቦታ ይወሰናል ።

ለምሳሌ ለውጥ ወይም አብዮት በሚባለው ጥያቄ ላይ ሰዎች የተለያዩ አስተሳሰቦች ይሰነዝራሉ ። አንዱ አብዮት መጥፎ ነው ይላል ። ሌላው ደግሞ አብዮት ጥሩ ነው ይላል ። ይህ ያስተሳሰብ ልዩነት ከየት መጣ ? የዚህ የአስተሳሰብ ልዩነት ምንጩ የተለያየ የሰዎች የኑሮ ሁኔታ ነው ።

« አብዮት መጥፎ ነው » ብለው የሚያስቡ ሰዎች እነማን ናቸው ? እነዚህ ሰዎች ንጉሣዊ ቤተሰቦች ፤ መሳፍንት ፤ መኳንንት ባለርስቶች የመሳሰሉት ናቸው ። እነዚህ ሰዎች በኅብረተሰቡ ኢኮኖሚ ውስጥ የተደላደለ የበዝባዥ ቦታ ይዘው ነበር ። ስለዚህ ኑሮዋቸው ለውጥ የሚያስፈልገው አልነበረም ። ስለሆነም ኑሮዋቸው አስተሳሰባቸውን ስለሚያፈልቅ አስተሳሰባቸው ለውጥን የሚፈልግ አልነበረም ። በዚህ የተነሣ ነው በነሱ አስተሳሰብ « አብዮት መጥፎ ነው » የሚባለው ።

« አብዮት ጥሩ ነው » ብለው የሚያስቡ ሰዎችስ እነማን ናቸው ? እነዚህ ደግሞ ጪሰኞች ፤ ድኃ ገበሬዎች ፤ ወዝአደሮች ፤ . . . . ወዘተ ናቸው። እነዚህ ሰዎች በኅብረተሰቡ ኢኮኖሚ ውስጥ የተበዝባዥ ቦታ የያዙና በኑሯቸው የተጐዱ ናቸው ። ስለሆነም ኑሮዋቸው ለውጥን ይፈልጋል ። የሚያስቡትም እንደኑሮዋቸው ስለሆነ በአስተሳሰባቸውም ለውጥን ይፈልጋሉ ማለት ነው ። በዚህ የተነሣ ነው እነሱ ደግሞ « አብዮት ጥሩ ነው » የሚሉት ።

ማርክስ ይህንን ሐቅ ለማስረዳት ነው « በኅብረተሰብ ውስጥ የሰዎችን የኑሮ ሁኔታ የሚወስነው አስተሳሰባቸው አይደለም ፤ አስተሳሰባቸውን የሚወስነው የኑሮዋቸው ሁኔታ እንጂ » ብሎ ያለው ።

ስለሆነም ሰዎች በኅብረተሰብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በጽሑፍ ፤ በንግግር ፤ በፖለቲካ በሥዕል በሙዚቃ ፤ በፍልስፍና ፤ በጠቅላላው በርእዮተ ዓለም መስክ አስተያየታቸውን በሚሰነዝሩበት ጊዜ እነዚህ አስተያየቶች እንዲሁ ከሰማይ ዱብ ያሉ ወይም ከአንጐላቸው ዝም ብለው ፈልቀው የወጡ እንዳይደሉና ከተጨባጭ ኑሮዋቸው የፈለቁ አስተሳሰቦች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

ይህም ስለተባለ የሰዎች አስተሳሰብ የኑሮ ሁኔታቸውን ለመለወጥ ፈጽሞ አይረዳም ማለት አይደለም ። አስተሳሰብም በኑሮ ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ አለው ሁለቱም ተያይዘው ነው የሚያድጉት የሚለወጡት ። ማርክሲዝም የሰዎች አስተሳሰብ ተጨባጭ ኑሮዋቸው ላይ ምንም ተጽእኖ አያደርግም አይልም ። ያደርጋል ። የተባለውም ቁስ አካል ከሃሳብ እንደሚቀድመው ሁሉ በኅብረተሰብም ውስጥ የሰዎች ተጨባጭ ኑሮ አስተሳሰባቸውን ይገዛል ነው ። ተጨባጩ የኑሮ ሁኔታ ተቀዳሚነት አለው እንጂ የሰዎችን አሳብ በኑሮዋቸው ላይ ፈጽሞ ተጽእኖ የለውም ማለት አይደለም ።

በተጨማሪ በቁስአካላዊነት አስተሳሰብ ማንኛውም ነገር የሚያድገው ጠቅላላ እንቅስቃሴ እራሱ በውስጡ በያዛቸው ቅራኔዎች ትግል እንደሆነ አይተናል ። በኅብረተሰብም ውስጥ የሚደረጉት ለውጦች በዚያው በኅብረተሰቡ ውስጥ ባሉ ቅራኔዎች ትግል እንጂ ከውጭ ወይም ከላይ ሆኖ በሚገፋፋ ኃይል እንዳይደለ ያምናል ። እንደዚህም ስለሆነ ስለሰው አመጣጥ ፤ ስለዝናብ ፤ ስለመብረቅ . . . ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሊረጋገጡ የሚችሉና ለሰው ጥቅም ሊውሉ የሚችሉ ሕግጋት ማግኘት እንደሚችለው ሁሉ ስለኅብረተሰቦችም አስተዳደግ ስለለውጥ ስለአብዮት . . . ያንኑ ኅብረተሰብ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አጥንቶ ተጨባጭ ሕጎችን ማግኘትና በነሱም በመጠቀም ትግሉን ማካሔድ ይቻላል ይላል ። ይህ ደግሞ የማርክስ ፍልስፍና ሁለተኛ አካል ወደ ሆነው ወደዲያሌክቲክስ የለውጥ ሕግጋት ያመጣናል ።

( ይቀጥላል )